የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰፍኛ ዓመት ቁጥር ፲፪
አዲስ አበባ የካቲት ፩ ቀን ፪ሺ፲፰

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32nd Year No. 12
ADDIS ABABA, 11th February, 2026

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፹፭/፪ሺ፲፰

የሁሉን አቀፍ የተደራሽነት ፈንድ የገቢ መጠን፣ ምንጭ እና አስተዳደርን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ .....

.....ገጽ ፲፱፻፫፻፫፫

Content

Regulation No.585/2026

Council of Ministers Regulation for determining the amount, source and administration of Universal Access Fund .....

.....Page 19503

ደንብ ቁጥር ፭፻፹፭/፪ሺ፲፰

የሁሉን አቀፍ የተደራሽነት ፈንድ የገቢ መጠን፣ ምንጭ እና አስተዳደርን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሁሉን አቀፍ የተደራሽነት ፈንድ በሕግ በመቋቋሙና የፈንዱን የገቢ መጠን፣ ምንጭ እና አስተዳደርን ለመወሰን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ እንደሚያወጣ የተደነገገ በመሆኑ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶፭/፪ሺ፲፩ አንቀፅ ፶፱ ንዑስ አንቀፅ (፫) መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

REGULATION No. 585/2026

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO DETERMINE THE AMOUNT, SOURCE AND ADMINISTRATION OF UNIVERSAL ACESS FUND

WHEREAS, the Universal Access Fund has been established by law, and the Council of Ministers is mandated to issue Regulation that govern the amount, sources and management of the Fund;

NOW, THEREFORE, this Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 49 Sub-Article (3) of the Communications Service Proclamation No.1148/2019.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 470.10

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የሁሉን አቀፍ የተደራሽነት ፈንድ የገቢ መጠን፣ ምንጭ እና አስተዳደርን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፹፭/፪፻፸፫ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ዉስጥ፡-

፩/ "ፈንድ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፵፱ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት የተቋቋመው የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት ፈንድ ነው፤

፪/ "ፈቃድ" ማለት ባለሥልጣኑ ለኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦት የሚሰጠው ፈቃድ ነው፤

፫/ "ባለፈቃድ" ማለት የኮሙኒኬሽን አገልግሎት እንዲሰጥ በባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

፬/ "መክፈል ወይም መሥራት" ማለት ባለፍቃዶች የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት ፕሮግራም ግዴታን በሕግ የተቀመጠውን የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት መዋጮ መጠን በመክፈል ወይም ተመጣጣኝ የሆነ የሁሉን አቀፍ ግብ የሚያሳኩ አገልግሎቶችን እና መሠረተ ልማቶችን በራስ በመስራት የሚወጡበት ዘዴ ነው፤

፭/ "አዋጅ" ማለት የኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር ፩፻፩፻፵፯/፪፻፲፩ ነው፤

PART ONE

GENERAL

1. Short Title

This Regulation shall be cited as the "Council of Ministers Regulation No. 585/2026 for determining the amount, source and administration of Universal Access Fund."

2. Definitions

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ **"Fund"** means the Universal Access Fund established under Article 49, Sub-Article (3) of the Proclamation;

2/ **"License"** means a license issued by the Authority for the provision of communications services;

3/ **"Licensee"** means a person who has been issued a license by the authority for the provision of communication services;

4/ **"Pay-or-Play"** means a mechanism whereby licensees carry out their universal service program obligations either by paying a legally determined universal access levy or by providing proportional services and infrastructures that aligns with established Universal Access objectives;

5/ **"Proclamation"** means the Communications Service Proclamation No. 1148/2019;

፮/ "ድጎማ" ማለት የሁሉን አቀፍ የተደራሽነት እና አገልግሎት ፕሮግራምን ወይም ፕሮጀክትን ለመደገፍ በገንዘብ ወይም በዓይነት የሚሰጥ ድጋፍ ነው፤

6/ "Subsidies" means financial or in-kind assistance granted to support Universal Access programs or projects;

፯/ "ግብ ተኮር ድጎማ" ማለት ተጨማሪ ወይም ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ሳይኖር ኪሳራ የሚያስከትሉ አገልግሎቶችን በረጅም ጊዜ ቀጣይነት ወዳለው ትርፍ ምጣኔ የሚያመጣ ለኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪዎች ከፈንዱ የሚሰጥ የአንድ ጊዜ የገንዘብ ድጋፍ ነው፤

7/ "Smart Subsidy" means a one-time amount of financial support that will bring loss-making services to a sustainable rate of return over the long term for communications Service provider, meaning that no further or recurring support will be required from the Fund;

፰/ "የቴሌኮሙኒኬሽን የመደብ ፍቃድ" ማለት የግል ፈቃድ ማውጣት ሳያስፈልግ የፈቃድ መሠረታዊ ድንጋጌዎች እና ሁኔታዎችን ለሚያሟላ ማንኛውም ሰው የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ለመስጠት እና/ወይም ፍሪኩዌንሲን ለመጠቀም የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

8/ "Telecommunications Class License" means a license that authorizes any Person that complies with the basic terms and conditions of the authorization to provide a telecommunications service and/or use frequencies without the need for an individual license;

፱/ "ሁሉን አቀፍ አገልግሎት" ማለት በባለሥልጣኑ በተወሰነው የአገልግሎት ጥራት ደረጃ መሠረት ያለ ምንም ልዩነት ለሁሉም ሰው የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ማቅረብ ሲሆን አገልግሎቱ በተመጣጣኝ ዋጋ እና በግለሰብ፣ በቤተሰብ ወይም በተቋም ደረጃ በግል በሚደረግ የደንበኝነት ምዝገባ የሚገኝ ይሆናል፤

9/ "Universal Service" means the provison of communications services, without discrimination on any basis, to everyone consistent with the quality of service specified by the Authority, and the services become available with affordable price and private subscription on individual, household or institutional basis;

፲/ "በቂ አገልግሎት የሌለባቸው አካባቢዎች" ማለት ባለሥልጣኑ ዝቅተኛ ተፈላጊ ደረጃ ብሎ ካስቀመጠው የአገልግሎት ጥራት ደረጃ በታች የሆኑ የአገልግሎት ተደራሽነት ያላቸው መልክአ-ምድራዊ ቦታዎች ናቸው፤

10/ "Underserved Areas" means geographic areas where the existing level of access is below the quality of service defined by the Authority as the minimum required standard;

CamScanner

፲፩/ "አገልግሎት ያልደረሰባቸው አካባቢዎች" ማለት ባለሥልጣኑ ባስቀመጠው ደረጃ መሰረት ምንም ዓይነት የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት የሌለባቸው መልክአ-ምድራዊ ቦታዎች ናቸው፤

11/ **"Unserved Areas"** means geographic areas where no level of Universal Access as defined by the authority is currently available;

፲፪/ "መዋጮ" ማለት ባለሥልጣኑ ለሁሉን አቀፍ ተደራሽነት ፈንድ ዓላማ ከባለፍቃዶች የሚሰበሰበው መዋጮ ነው፤

12/ **"Levy"** means a levy the Authority collects from licensees for purposes of the Universal Access Fund;

፲፫/ "የተጣመረ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ፈቃድ" ማለት የሽቦ ወይም መዳብ፣ ፋይበር፣ ኬብል፣ ገመድ አልባ እና የሳተላይት ማስተላለፊያ ማዞሪያዎችን ጨምሮ የዓለም አቀፍ መውጫ በር፣ የኢንተርኔት ማዞሪያ እና ማንኛውንም የኤሌክትሮኒክ ኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ለመስጠት በሚችል ቴክኖሎጂ የኢንተርኔት ቴሌፎንን ጨምሮ የድምጽ፣ የዳታ፣ የጽሁፍ እና የቪዲዮ አገልግሎቶችን የቴክኖሎጂ እና የአገልግሎት ገለልተኝነት መርሆዎችን በተከተለ መልኩ በኢትዮጵያ ውስጥ በማንኛውም ሥፍራ ማንኛውንም የሞባይልና የመደበኛ ወይም ቋሚ ኔትዎርኮችን ለማቀድ፣ ለመገንባት፣ ለማከናወን እና ለማስቀጠል እንዲሁም የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ እና ለመቀበል የሚያስችል በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

13/ **"Unified Telecommunications Operator License"** means a License issued by the Authority for the planning, building, operating, and maintaining of any mobile and fixed networks that includes copper, fiber, cable, wireless, satellite switched networks, international gateways, internet exchanges and technology capable of offering any electronic communication services including, but not limited to, voice inclusive of internet telephony, data, text, and video embracing the principles of technology and service neutrality anywhere within Ethiopia, and to send and receive Telecommunications services to and from outside Ethiopia;

፲፬/ "ፕሮግራም" ማለት በባለሥልጣኑ የተቀመጡ የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት እና አገልግሎት ግቦችን ለማሳካት የሚያስችሉ ፈንዱን መሰረት ያደረጉ የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት እና አገልግሎት ፕሮግራሞች ናቸው፤

14/ **"Programs"** means the Universal Access and service initiatives initiated by the Fund aimed at achieving the Universal Access and service objectives established by the Authority;

CamScanner

፲፫/ "ፕሮጀክት" ማለት ከእያንዳንዱ የሁለን አቀፍ ተደራሽነት ፕሮግራም ጋር የተያያዘ ዝርዝር ተግባራት ያሉት ፕሮጀክት ነው፤

፲፬/ በእዋኋ የተሰጡት ትርጓሜዎች በዚህ ደንብ ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

15/ **"Projects"** means the specific micro-level implementation activities related to each Universal Access program;

16/ The definitions given by the Proclamation shall be applicable to this Regulation.

፫. የፈንዱ ዓላማዎች

ፈንዱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ በሀገሪቱ ውስጥ በተለይም በገጠራማ እና ርቀት ላይ በሚገኙ አገልግሎት ባላገኙ ወይም በቂ አገልግሎት በሌለባቸው አካባቢዎች የኮሙኒኬሽን መሰረተ ልማት እና አገልግሎት ማስፋፋት እና ትስስር እንዲፈጥሩ ማስቻል፤

፪/ በሁሉም ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ የሚገኙ ማህበረሰቦች በተለይም አካል ጉዳተኞች፣ ሴቶች እና ሌሎች ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የአገልግሎት ተደራሽነት እንዲያገኙ ማስቻል፤

፫/ የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት ግብን ሊያሳኩ የሚችሉ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂዎችን፣ ምርምሮችን እና ፈጠራዎችን መደገፍ፤

፬/ በትምህርት ቤቶች፣ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ በጤና አውታሮች እና ሌሎች ሕዝብን የሚያገለግሉ ተቋማትን ጨምሮ ዘርፍ ተኮር የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ በማድረግ ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል፤ እና

፭/ የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት ግብ ሊያሳኩ የሚችሉ የሀገራዊ ይዘት ልማትን እና ሌሎች መሰል ተግባራትን መደገፍ።

3. Objectives

The objectives of the Fund shall include the following:

1/ Ensure the expansion and integration of communications infrastructure and services in Ethiopia, in particular to rural and remote unserved and underserved areas;

2/ Ensure availability of services to all socio-economic segments of society, in particular person with disabilities, women and other vulnerable groups;

3/ Support information and communications technologies and innovations that aim to achieve the objectives of the Universal Access goal;

4/ Support sectoral expansion of ICT services, including, but not limited to schools ,higher education, health facilities and other organizations serving public needs, and make them provide efficient service;and

5/ Support the development of local content and other related activities which will achieve the Universal Access goal.

CamScanner

ክፍል ሁለት

የፈንዱ ምንጭ እና አስተዳደር

፬.የባለሥልጣኑ ፈንዱን የማስተዳደር ሥልጣን እና ተግባር

ባለሥልጣኑ ፈንዱን ከማስተዳደር ጋር በተያያዘ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በሁሉን አቀፍ ተደራሽነት እና የአገልግሎት ግዕቀፍ ውስጥ በተቀመጡ መስፈርቶች መሰረት የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት ፈንድን ይሰበስባል፣ ያስተዳድራል፣ ሥራ ላይ ያውላል፣

፪/ የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት ስትራቴጂክ እቅድ ያዘጋጃል፣

፫/ የፈንዱን ዓመታዊ የትግበራ እቅድ ያዘጋጃል፣

፬/ ከፈንዱ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ መልክዓ-ምድራዊ ቦታዎችን፣ የህብረተሰብ ክፍሎችን እና ተቋማትን ለመለየት የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸው የማህበረ-ኢኮኖሚያዊ መስፈርቶችን ያዘጋጃል እንዲሁም ግልጽ፣ ከአድሎ ነጻ የሆነ እና በውድድር ላይ የተመሰረተ የመምረጫ ሂደት ይተገብራል፤

፭/ በአግባቡ ሀብት የሚሰበሰብበትን እና ፈንዱ የሚተዳደርበትን አስተዳደራዊ ስልቶች፣ ሥርዓቶች እና መዋቅሮች ይዘረጋል፤

PART TWO

SOURCE OF THE FUND AND FUND ADMINISTRATION

4. Authority's Fund Administration Powers and Duties

The Authority shall have the following powers and duties in relation to Fund administration:

1/ Collect, administer and execute the Universal Access Fund consistent with the Universal Access and service framework requirements;

2/ Develop a Universal Access strategic plan;

3/ Develop annual operating plans for the Fund;

4/ Develop appropriate socio-economic criteria for identifying the geographical areas, population groups, institutions and organizations that may be eligible to benefit from the Fund, and apply open and non-discriminatory competitive selection process;

5/ Establish administrative mechanisms, systems and structures for proper collection of resources and management of the Universal Access Fund;

CamScanner

፮/ የሁሉ አቀፍ ተደራሽነት ነባራዊ ሁኔታን እንዲሁም ቀጣይ እድገትን ለማረጋገጥ የተከናወኑ ስራዎችን ለመገምገም የሚያስችሉ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ተደራሽነት ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾችን ያዘጋጃል፤

6/ Develop specific key performance indicators of communications access to assess status and progress in the achievement of Universal Access;

፯/ ከፈንዱ ላይ የፋይናንስ ድጋፍ እንዲደረግላቸው የቀረቡ የፕሮጀክት ሀሳቦችን መገምገም የሚያስችሉ ግልጽ መስፈርቶችን ያዘጋጃል፤

7/ Develop a clearly defined set of criteria for evaluating project proposals submitted for funding;

፰/ በፈንዱ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች የጨረታ ሰነድ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ መስፈርቶችን ይለያል ፤እና

8/ Develop criteria to be published in the tender documents of projects supported by the fund; and

፱/ የፈንድ ድጎማ የተደረገላቸውን ፕሮጀክቶች ክንውኖችን ይገመግማል፣ ይቆጣጠራል።

9/ Monitor and evaluate fund projects with subsidery.

፭. <u>የፈንዱ ምንጭ</u>

ፈንዱከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፦

5. <u>Sources of the Fund</u>

The sources of the Fund shall comprise the following:

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ከኮሙኒኬሽን አገልግሎት ባለፈቃዶች የሚሰበሰብ መዋጮ፤

1/ A Universal Access levy collected from communications service licensees, in accordance with Article 7 Sub-Article (1) of this Regulation;

፪/ ከልማት አጋሮች የሚገኝ ስጦታ ፤እና

2/ Grants from development partners; and

፫/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት በፈንድ አካውንት ውስጥ የሚቀመጠውን ትርፍ ገንዘብ ኢንቨስትመንት ላይ በማዋል የሚገኝ ገቢ።

3/ Income from investment of surplus funds in the Fund's operating account in accordance with Article 16, Sub-Article (2) of this Regulation.

፮. ለፈንዱ መዋጮ ስለሚያደርጉ ባለፍቃዶች

፩/ ባለሥልጣኑ የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት መዋጮን የተጣመረ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ባለፍቃዶችን ጨምሮ የህዝብ ቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት በንግድ አገልግሎት መሠረት ከሚሰጡ ከሁሉም የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ባለፍቃዶች ላይ በየዓመቱ ይሰበስባል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ባለፍቃዶች ከፈንድ መዋጮ ነጻ ሊያደርግ ይችላል፦

ሀ) የሁሉን አቀፍ አገልግሎት ተደራሽነት ግዴታ ያለበት የህዝብ ብሔራዊ የፖስታ አገልግሎት ባለፈቃድ፣

ለ) ያለምንም የትርፍ ሕዳግ በተወሰነ አካባቢ አገልግሎት የሚሰጡ የማህበረሰብ ኔትወርክ አገልግሎት ባለፍቃዶች፣

ሐ) የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፍቃድ ኖሯቸው አገልግሎቱን ለግል የሚጠቀሙ ባለፍቃዶች፣ ወይም

መ) ባለሥልጣኑ በመመሪያ የሚለያቸው ሌሎች ባለፍቃዶች።

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ባለሥልጣኑ በመመሪያ በሚወስነው የካፒታል አቅም ላይ እስኪደርሱ ድረስ የቴሌኮሙኒኬሽን የመደብ ፍቃድ ባለቤቶች፣ ጀማሪ የንግድ ሥራ አልሚዎች ወይም የፈጣን ፖስታ አገልግሎት ባለፈቃዶች የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት መዋጮ እንዳይከፍሉ ሊያደርግ ይችላል።

6. Licensees' Contribution to the Fund

1/ The Authority shall collect the Universal Acess levy from all communications service licencees, including Unified Telecommunications licensees, that provide public telecommunications service on a commercial basis, annually.

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, the Authority may exempt the following licensees from the levy charges:

a) National postal service license holder, which has a universal access obligation;

b) Community network service license holder, which provides service in a limited area without any profit margin;

c) Communications license holders, which operate communications for their own use;or

d) Other licensees that the authority may determine by a Directive.

3/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, telecommunications class license holders, startups, business developers or express mail service licensees may be relieved from levy charges until they reach the capital amount that the authority will determine by a Directive.

CamScanner

፮.የፈንዱ የመዋጮ መጠን

፩/ ለፈንዱ መዋፅ የሚያደርጉ ባለፈቃዶች ከኮሙኒኬሽን አገልግሎት ከሚያገኙት አጠቃላይ ዓመታዊ ገቢ ላይ በየዓመቱ አንድ ነጥብ አምስት በመቶ ለፈንዱ መክፈል አለባቸው።

፪/ ባለሥልጣኑ ለሁሉም አዲስ ባለፈቃዶች ፈቃዱን ካገኙበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሦስት (፫) ዓመት የሚደርስ የፈንድ መዋፅ የመክፈያ የእፎይታ ጊዜ ይሰጣል።

፯.የፈንዱ መዋጮ መጠን ላይ ሊደረግ ስለሚችል ለውጥ

ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መክፈል ወይም መስራት የሚለውን መርህ በመጠቀም በባለሥልጣኑ የተለዩ እና የጸደቁ የፈንዱን ግቦች የሚያሳኩ የካፒታል ፕሮጀክቶችን ለመገንባት እና አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል ባለፍቃዱ ካወጣቸው ወጪዎች ውስጥ ባለስልጣኑ ድጋፍ አደርጋለው ብሎ ያሳወቀው የወጪ መጠን ከሁሉን አቀፍ ተደራሽነት መዋጮ ላይ ተቀናሽ ያደርጋል።

፰.ፈንዱ የሚሰበሰብበት ጊዜ

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተመለከተው መዋጮ ባለፍቃዶች የበጀት ዓመቱ ካለቀበት ጊዜ ጀምሮ በሶስት (፫) ወራ ት ጊዜያት ውስጥ የሚያቀርቡትን ዓመታዊ የፋይናንስ ሪፖርት መሰረት በማድረግ እየተሰላ በየዓመቱ መሰብሰብ አለበት።

7. Levy Amount

1/ The licensees which are supposed to pay the levy to the Fund shall pay one and half percent (1.5%) from their gross annual revenue for the provision of communications services every year.

2/ The Authority shall grant a grace period of up to Three (3) years to all new entrant licensees starting from the effective date of their license, prior to commencement of the collection of levy payments.

8. Variations in the Amount of the Universal Access Levy

Where appropriate, the authority shall deduct from the Universal Access levy contribution the deemed subsidy costs incurred by a licensee to build and operate capital projects that the authority has identified and approved as meeting the requirements of the Universal Access objective under the pay-or-play provision.

9. Levy Collection Period

1/ The levy which is indicated in Article 7 Sub-Article (1) of this Regulation shall be collected annually, in arrears, calculated from the annual financial reports which shall be submitted by the licensee within Three (3) months following the end of the financial year.

CamScanner

ሸ/ ለፈንዱ ዓላማ የበጀት ዓመት ማለት ከሐምሌ ፩ ቀን ጀምሮ እስከ ቀጣዩ ዓመት ሰኔ ሰላሳ (፴) ቀን ድረስ ያለው ወቅት ነው፡፡

ቀ/ ባለሥልጣኑ ዓመታዊ የባለፍቃዱ የፋይናንስ ሪፖርት በደረሰው በሰላሳ (፴) ተከታታይ ቀናት ውስጥ የመዋጮውን መጠን በማስላት ለባለፍቃዱ ማሳወቅ አለበት፡፡

በ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ቀ) መሰረት የመዋጮ መጠን የተላከለት ባለፍቃድ ክፍያውን የፈንድ መዋጮ መጠን ማሳወቂያው በደረሰው በሰላሳ (፴) ተከታታይ ቀናት ውስጥ መክፈል አለበት፡፡

፲. <u>የፈንድ መዋጮ ክፍያ አለመፈፀም</u>

፩/ ዓመታዊ የፈንድ መዋጮውን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ እና ፱ መሠረት ያልከፈለ ባለፈቃድ፡-

ሀ) ክፍያውን ሊፈፅም ከሚገባው ቀን ገደብ እስከ አንድ (፩) ወር ጊዜ እንዲዘግይ ካደረገ ያልተከፈለውን መዋጮ ሁለት ፐርሰንት ፣እና

ለ) በቀጣይነት ክፍያው እስከሚፈፀም ድረስ ለተጨማሪ ጊዜያት በየወሩ ያልተከፈለውን መዋጮ አምስት ፐርሰንት ፣ ይከፍላል፡፡

2/ The Financial year for the purposes of the Fund commences from July 8 and ends on July 7 of the following year.

3/ The Authority shall calculate the amount of levy and notify the amount to the licensee within thirty consqutive days (30) from receipt of the annual financial report.

4/ The licensee that receives the notification of levy amount as outlined in Sub-Article (3) of this Article is required to pay the specified amount to the Authority within thirty (30) consqutive days of receipt.

10. <u>Failure to Pay Levy</u>

1/ A Licensee who fails to pay the Universal Acess levy in accordance with Article 7 and 9 of this Regulation shall pay:

a) Two percent (2%) of the unpaid levy if the levy is not paid within one (1) month from the due date; and

b) Five percent (5%) of the amount of the unpaid levy for each additional month.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ለ) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የፈንድ መዋጮው በምንም ዓይነት ሁኔታ ከስድስት (፮) ወራት በላይ ሳይከፈል መቆየት የለበትም።

፫/ ባለሥልጣኑ የፈንድ ክፍያን በስድስት (፮) ወራት ውስጥ ያልከፈለ ባለፈቃድን ፈቃድ እንደ ሁኔታው ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል።

2/ Without prejudice to Sub-Article 1(b) of this Article, the levy shall not stay unpaid in any case for more than Six (6) months.

3/ The Authority as the case may suspend or revoke the License of the licensee if the licensee doesn't pay its levy within Six (6) months of the due date.

ክፍል ሦስት

የፈንዱ አጠቃቀም

PART THREE

FUND UTILIZATION

፲፩. ፈንዱ የሚከፋፈልበት መንገድ

ባለሥልጣኑ የዚህን ደንብ አንቀጽ ፲፪ መሠረት በማድረግ የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞችን በሚከተለው መልክ ይደግፋል፦

ሀ) በድጎማ፣ ወይም

ለ) በስጦታ

11. Means of Funding

The Authority shall fund, as per Article 12 of this Regulation, Universal Access programs and projects through:

a) Subsidies; or

b) Grants

፲፪. በፈንዱ ድጋፍ የሚደረግላቸው ፕሮጀክቶች

፩/ የዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ እንደተጠበቀ ሆኖ ፈንዱ የሚከተሉትን ተግባራት ለመደገፍ ይውላል፦

ሀ) በፈንዱ የታቀፉ እና ተግባራዊ የሚደረጉ የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት መርሃ ግብሮችን እና ፕሮጀክቶችን፣

ለ) የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት ግብ የሚያሳኩ የግሉ ሴክተር ወይም የማህበረሰብ ኢንቨስትመንቶችን፣

12. Projects to be Supported by the Fund

1/ Without prejudice to Article 3 of this Regulation, the fund shall support the following activities:

a) Universal Access programs and projects that are initiated and implemented by the Fund;

b) Private sector or community investments which realize achievement of universal service objectives;

ሐ) ከሁሉን አቀፍ ተደራሽነት እና የፈንድ ፕሮግራም ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያላቸው በኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂዎች ዙሪያ የሚሰሩ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን፣ ስልጠናዎችን፣ የግንዛቤ ማስፈጠሚያዎችን እና መሰል ጉዳዮች ፣

c) Conducting research, studies, trainings, promotions and other activities in communications and information technologies which are directly related to Universal Access and the Fund's Programs;

፪/ ባለሥልጣኑ በፈንዱ የሚደገፉ ፕሮጀክቶችን በሚለይበት ወቅት፡-

2/ When identifying the projects to be funded by the Fund, the Authority shall consider:

ሀ) በግብ ተኮር ድጎማ አማካኝነት በአነስተኛ የአንድ ጊዜ ድጎማ የኮሙኒኬሽን መሰረተ ልማት፣ ሥርዓት እና የአገልግሎት ተደራሽነትን በውጤታማነት እና በዘላቂነት የሚያስፋፉ፣ እና

a) Projects that effectively and sustainably expand access to communications infrastructure, systems and services through "smart subsidies" with minimal one-time funding; and

ለ) የፈንድ ድጎማ ሳይደረግላቸው በኢኮኖሚ አዋጭ ሆነው መቀጠል የማይችሉ ፕሮጀክቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል።

b) Projects that are not economically feasible without support of the Fund.

፫/ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪዎች አስቀድመው አገልግሎት ተደራሽ ባደረጉባቸው እና ለንግድ አገልግሎት ባዋሉባቸው የገጠር እና ርቀት ያላቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች በቂ የአገልግሎት ተደራሽነት የሌለ መሆኑ ሲረጋገጥ ፈንዱ በእነዚህ አካባቢዎች የሚካሄድ የኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦትን ለመደገፍ ሊውል ይችላል።

3/ The Fund may be utilized to support the provision of communications services in rural and remote areas of the country where communications service providers have already made services accessible and commercially operational, provided that it is confirmed that there is insufficient service in those areas.

CamScanner

፲፫. በፈንዱ ድጋፍ የተዘረጉ መሠረተ ልማቶችን ስለመጋራት

በፈንዱ ለማካኝነት የኮሙኒኬሽን መሰረተ ልማት እንዲዘረጋ ወይም እንዲያሻሽል ድጋፍ የተደረገለት የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ እነዚህን መሰረተ ልማቶችን የመሠረተ ልማት መጋራት እና የኮሌኬሽን አትርቦት እንዲሁም የሮሚንግ አገልግሎት ለሚፈልጉ ሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች አግባብነት ያላቸውን ሕጎች መሰረት በማድረግ ተደራሽነት መስጠት አለበት።

ክፍል አራት

የፈንዱ ሒሳብ እና ዓመታዊ ሪፖርት

፲፬. የፈንዱ ሒሳብ

፩/ ባለሥልጣኑ ፈንዱን አንድ ወይም ከዛ በላይ በሆኑ ለዚህ ዓላማ ተብለው በጎንዘብ ሚኒስቴር እውቅና የተከፈቱ የፈንድ ሒሳቦች ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ እውቅና ባላቸው አንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ባንኮች ተቀማጭ ማድረግ አለበት።

፪/ ባለሥልጣኑ ለፈንድ የተለዩ ሒሳቦችን እንዲሁም ተገቢውን የሒሳብ ደብተር እና የፈንዱን የፋይናንስ አሰራር መዛግብት መያዝ አለበት።

፫/ የፈንዱ ሒሳብ በበጀት ዓመቱ ማብቂያ ላይ በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚወክለው ኦዲተር መመርመር አለበት።

13. Sharing of Infrastructures Developed with the Support of the Fund

A Communications Service Provider that is subsidized by the fund to develop or improve communications infrastructure shall provide open access to such infrastructure to other service providers that require commercial infrastructure sharing, collocation or national roaming services in accordance with the relevant Directives.

PART FOUR

FUND ACCOUNT AND ANNUAL REPORT

14. Fund Accounts

1/ The Authority shall deposit the funds into one or more dedicated accounts of the Universal Access Fund, which have been established with the acknowledgment of the Ministry of Finance, at one or more reputable banks in Ethiopia.

2/ The Authority shall maintain separate accounts for the Universal Access Fund and shall keep proper books of accounts and records of the operations of the Fund.

3/ The accounts of the Fund shall be audited by the Federal Auditor General or an Auditor designated by him at the end of each financial year.

CamScanner

፲፭. ዓመታዊ ሪፖርት

፩/ ባለሥልጣኑ የኢትዮጵያ የበጀት ዓመት ባበቃ በስድስት (፮) ወራት ጊዜ ውስጥ የሚከተሉትን መረጃዎች አካቶ ዓመታዊ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ስራ አመራር ቦርድ ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) የተመረመረ የፈንዱን የገንዘብ መግለጫ፤

ለ) በፈንዱ ድጋፍ የተደረገላቸው ተግባራት ዝርዝር፤

ሐ) በፈንዱ ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾች መሠረት የታለሙ የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት ግቦች ስኬት።

፪/ ባለሥልጣኑ በስራ አመራር ቦርዱ የጸደቀውን ፈንዱን የተመለከተ ዓመታዊ ሪፖርት በጸደቀ በአንድ (፩) ወር ጊዜ ውስጥ በተቋሙ ድረ-ገጽ ላይ ለሕዝብ ይፋ ማድረግ አለበት።

፲፮. የፈንዱ ኢንቨስትመንት

፩/ ፈንዱ ወቅታዊ እና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሁሉን አቀፍ ተደራሽነት ለማስፋፋት መዋል አለበት።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፈንዱ ለታቀደለት ዓላማ ከመዋሉ በፊት የፈንድ ሒሳብ ውስጥ ተከማችቶ የተቀመጠ ገንዘብን ባለሥልጣኑ፡-

ሀ) የጊዜ ገደብ ባለው የሒሳብ ዓይነት ለማስቀመጥ፤

ለ) ለመንግስት የዋስትና ሰነድ ግዥ፤ ወይም

15. Annual Report

1/ The Authority shall, within Six (6) months after the end of the Ethiopian financial year, prepare and submit to the Authority's Board of Management an annual report containing:

a) The audited financial statements of the Fund;

b) Details of activities supported by the Fund; and

c) Achievement of targeted Universal Access Objectives through the Fund's key performance indicators.

2/ The Authority shall publish its annual Fund-related report on its website within one (1) month of the report's approval by the Authority's Managment Board.

16. Investment of the Fund

1/ The Fund has to invest in universal access communications services in as timely and efficient manner as possible.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the Authority may invest or apply accumulated funds in the account, prior to its application to the prime purpose, in the following areas:

a) Fixed bank deposits;

b) Government securities; or

ሐ) በባለሥልጣኑ የስራ አመራር ቦርድ በጸደቀ ማንኛውም ኢንቨስትመንት ላይ ሊያውል፣ ይችላል።

c) Any other investments approved by the Authority's Board of Management.

፲፯. <u>ከፈንዱ ድጎማ እና አገልግሎት ውል ጋር የተያያዙ ግዴታዎች</u>

17. <u>Obligations Related to Fund's Subsidy and Service Contract</u>

፩/ ባለሥልጣኑ ውድድርን መሰረት ባደረገ መንገድ ከተመረጡና ድጎማ የተደረገላቸው ፕሮጀክቶችን ከሚያስተዳድሩ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪዎች ጋር ድጋፉ በአግባቡ ስራ ላይ የሚውልበትን ሁኔታ እና አፈጻጸም በተመለከተ አስገዳጅ ውል መግባት አለበት።

1/ The Authority shall enter into a legally binding subsidy agreement with competitively selected service providers that manage the subsidized projects, outlining the terms and conditions for the proper utilization of the fund and the execution of the contract for subsidized communications services.

፪/ ባለሥልጣኑ ውድድርን መሰረት ባደረገ መንገድ የተመረጡ ድጎማ የተደረገላቸው ፕሮጀክቶችን የሚያስተዳድሩ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪዎች ውሉ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የውሉን ሁኔታ እና ግዴታ ማክበራቸውን ማረጋገጥ አለበት።

2/ The Authority shall ensure that communications service providers who are awarded subsidized service contracts for Universal Access projects through its competitive procedures shall comply with all of the terms and obligations of their respective contracts during the full period they are in force.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ድጎማ የተደረገላቸው ፕሮጀክቶችን የሚያስተዳድሩ አገልግሎት ሰጪዎች ውሉ በስራ ላይ ባለበት ወቅትም ሆነ ከዚህ በኋላ የአገልግሎት ጥራት መስፈርቶችን ጨምሮ በፍቃዳቸው ውስጥ ለተገለጹ ሁኔታዎች ተገዥ መሆን አለባቸው።

3/ Without prejudice to Sub-Article (2) of this Article, service providers, both during and following the compliance period of their universal access fund contract, shall remain subject to the terms of their license, including quality of service requirements.

CamScanner

፬/ ማንኛውም አገልግሎት ሰፊ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ድንጋጌ ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ በውሉ እንዲሁም በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተመለከቱ ቅጣቶች ተፈጻሚ ይሆኑበታል።

4/ Any Service providers who violates Sub-Article (2) and (3) of this Article shall be penalized in accordance with the terms of their contract and other appropriate laws.

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

PART FIVE

MISCELLANEOUS

፲፰.ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

ከዚህ ደንብ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ደንብ፣ መመሪያ እንዲሁም የአሰራር ሥርዓት በዚህ ደንብ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

18. Inapplicable Laws

No Regulation, Directive or Customary Practice which is inconsistent with the provision of this Regulation shall be applicable with regard to matters covered under the Regulation.

፲፱. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ባለሥልጣኑ ይህን ደንብ ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

19. Power to Issue Directives

The Authority shall have the power to issue Directives to execute this Regulation.

፳. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

20. Effective Date

This Regulation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazette.

አዲስ አበባ የካቲት ፩ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

Done in Addis Abeba , on this 11th day of February , 2026

ዐብይ አህመድ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

ABIY AHMED (Dr.)

PRIME MINISTER OF

THE FEDERAL DEMOCRATIC

REPUBLIC OF ETHIOPIA

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ